# በSY24-25 የኩሌጅ (Coolidge) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ: የመግቢያ ሂደት የደረጃ መጠን (Admissions Process Rubric) ለክፍል-ደረጃዎች: 9 እና 10

ስለ ቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ የመግቢያ **(Admissions)** መስፈርት:
በኩሌጅ (Coolidge) ውስጥ - የቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ፣ **'COLTS'** መሆን የሚፈልጉ ምሁራኖችን ይፈልጋል:

> የቀለም ትምህርት ግቦቻቸውን ለማሳካት እና ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ውስጥ ጥብቅ-በሆነ ሁኔታ እና በጽናት ራስን ማስተካከል የሚጠይቅ ቁርጠኝነት **(Committed)**።
> ስለእነርሱ እና ስለእኩዮቻቸው የማደግ ችሎታ ብሩህ አመለካከት ያላቸው **(Optimistic)**።
> ታማኝነትን፣ ተጠያቂነትን፣ እና የትምህርት ቤታችንን ማህበረሰብ - እሴቶችን መሪዎች በመሆን **(Leader)** የሚሸከሙ።
> በሚያደርጉት እርምጃዎች ላይ አስተዋይ-በመሆን እና በዓለም ላይ አዎንታዊ አስተዋጽዖ ለማምጣት በመስራት ህብረተሰብን መቀየር **(Transforming Society)**።

ስለ ቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ የመግቢያ-ሂደት **(Early College Academy (ECA) Admissions Process)**:
የመቀበያ ሂደታችን የሚያካትተው ሁሉን አቀፍ የሆነ ምልከታ ለእያንዳንዱ የማመልከቻ ክፍሎች - ሪፖርት ካርዶች፣ ጽሁፍ (essay)፣ እና የአስተማሪ ድጋፍ መስጫዎች (recommendations)። እያንዳንዱ የማመልከቻው ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሰረት ተገምግሟል። ምንም አንድ ክፍል፣ ብቻውን ለብቁነት መወሰኛ ሆኖ አይወሰድም። በቀለም ትምህርት ፕሮግራም ጥብቅነት ምክንያት፣ በGPA ላይ ከፍተኛ አፅንዖት የምንሰጠው እና በቀለም ትምህርት እድገት ላይ ወደላይ ሲያሻቅብ ማየትን የምንመርጠው ይሆናል። በጣም ስኬታማ ሆነው ያገኘናቸው አመልካቾች፣ ፈታኝ-ለሆነ ስራ ቁርጠኝነት ያላቸው ሲሆን ይህንንም በጽሁፋቸው (essay)፣ በድጋፍ መስጫዎች (recommendations) እና በቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ በተጨማሪነት ማስመስከር የቻሉ ናቸው።

እያንዳንዱ የማመልከቻ ሂደት ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሠረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚለካ ይሆናል። ሊገኝ-ከሚችለው ከ100 ውስጥ፣ 85 ነጥቦችን ያገኙ አመልካቾች ብቁ ይሆናሉ፤ ሆኖም ይህ ቁጥር ሁሉን-አቀፍ በሆነው የአመልካቾች ምልከታ ላይ መሠረት በማድረግ፣ ዓመታዊ የዝቅተኛ ደረጃ የሚስተካከልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል።

| የመግቢያ ክፍሎች **(Admissions Component)** | መለኪያ **(Weight)** | ማስታወሻዎች |
|---|---|---|
| የቀለም ትምህርት የመስፈርት ምልከታ (GPA) | 40 ነጥቦች | ECA ውጤቶችን (GPA) እንደ የቀለም ትምህርት መስፈርት ምልከታ አንዱ አካል አድርጎ ይመለከተዋል። በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) የGPA መስፈርት የለም። ተማሪዎች፣ ለSY22-23 የመጨረሻ ሪፖርት ካርዳቸውን እና ለSY23-24 የመጀመሪያ-ተርም ሪፖርት ካርድን ማስገባት አለባቸው። የሪፖርት ካርድ/የትምህርት ውጤት ማረጋገጫ እና ውጤቶች፣ ለማመልከቻው የመግቢያ (admission) ሂደት ከግምት ውስጥ እንዲገቡ መግባት አለባቸው።<br><br>ከ'ELA'፣ ሣይንስ፣ ሂሳብ፣ እና ኅብረ-ትምህርት (Social Science)/ታሪክ (History) የተገኙ የደረጃ-ውጤቶች፤ 'GPA'ን በማስላት-ላይ ጥቅም-ላይ ውለዋል። በተለምዶ፤ በ'ELA' ስኬታማ-የሆኑ ተማሪዎች - የ3.0 ወይም ከዚያ በላይ-የሆነ 'GPA' አላቸው። |



1200 First Street, NE | Washington, DC 20002 | T 202.442.5885 | F 202.442.5026 | dcps.dc.gov

| | | |
|---|---|---|
| የድጋፍ መስጫዎች (Recommendations) | 20 ነጥቦች | ‘ECA’፣ ሁለት (2) - የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) - ያስፈልገዋል። ECA፣ የአስተማሪ ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations)፣ ለተማሪዎች የአካዳሚክ መዝገብን፣ የጥረታቸውን ደረጃ፣ እና አጠቃላይ በትምህርት ቤት ውስጥ ያላቸውን ተሞክሮ ይዘትን ለመስጠጥ ይጠቀምበታል። በየግል የገቡ የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) በራሳቸው በኩል እንዲከታተሉ እና የድጋፍ ሰጪው የተማሪውን በእጅጉ የተሟላ ምስል እንዲያስገቡለት ለማድረግ፤ ተማሪዎች እና ቤተሰቦችን ክትትል እንዲያደርጉ አጥብቀን እናበረታታል። ሆኖም፣ ተማሪዎች ላልተሟሉ ወይም ለጠፉ የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ቅጣት አይደርስባቸውም፤ ስለሆነም፤ በተገኘው የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ላይ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ እንዲገመገም ይደረጋል። |
| የመፃፍ ማነቃቂያ (Writing Prompt) | 25 ነጥቦች | የመፃፍ ማነቃቂያ (writing prompt)፤ የተማሪን ፍላጎት እና የችሎታ ደረጃን ለማግኘት ይጠቅማል። የመቀበያው (admissions) ቡድኑ የተማሪውን በECA ውስጥ ያለውን ፍላጎት፣ ለመማር ያለውን ቁርጠኝነት፣ እና የወደፊት ግቦችን ለመለካት ጽሁፉን (essay) ይመለከታል። የመፃፍ ማነቃቂያ (writing prompt) በተጨማሪም - እንደ የተማሪው ሰዋሰው (grammar)፣ ቃላት (vocabulary) እና ቴክኒካል የአፃፃፍ ደረጃ፣ የመጀመሪያ ናሙና ሆኖ ጥቅም-ላይ ይውላል። |
| የቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ | 15 ነጥቦች | የቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ፣ የመጀመሪያ የሆነ ግንኙነቶችን የምንገነባት እና በማመልከቻ ሌሎች ገጽታዎች ላይ ጎልተው ለመመልከት ያልቻልናቸውን ነገሮች ለማወቅ እድል የሚሰጠን ነው። ‘ECA’፣ ተማሪዎች ወደ ቃለ-መጠይቁ፤ ከቤተሰብ አባል ጋር (ከወላጅ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ፣ የቅርብ የቤተሰብ አባል) ወይም ሌላ በህይወቱ ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ሰው ጋር (እንደ አሰልጣኝ፣ አማካሪ፣ ወይም የሕይወት-መካሪ/mentor)፤ ተማሪዎችን በመደበኛነት ከሚረዷቸው ጋር፣ አብረው እንዲካፈሉ ይፈልጋል። የቃለ-መጠይቁን ጨርሰን ስንወጣ፣ የተማሪውን ማንነት በተሻለ-ሁኔታ የምንረዳበት እና ቤተሰቡ እንዴት መማርን እንደሚደግፉ ለማወቅ እንደሚያስችለን ተስፋ አለን።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY24-25 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (virtually)፣ ሊከናወን ይችላል። የጤና መመሪያን በመከተል እና በመቆጣጠር ላይ፣ ቁርጠኛ ሆኖ መስራቱን - DCPS ይቀጥልበታል። |
| በማመልከቻው ውስጥ የሚገኙት ሁሉም ይዘቶች፣ ሊገኝ-የሚችለውን - የ**100** ነጥቦች**/points**ን አጠቃላይ-የውጤት ደረጃን ለመፍጠር፣ ተጨምሯል። ሁሉም ብቁ-የሆኑ ተማሪዎች፣ በ**‘My School DC’** ሎተሪ ውስጥ፣ ብቁነትን ለመወሰን፣ በአጠቃላይ የውጤት-ደረጃቸው ላይ ደረጃ-የሚሰጠው **(ranked)** ይሆናል። | | |